
# የአይፓድ/iPad ማብራሪያ መመሪያ



Amharic

Assistive Technology Lab
COMMUNITY VISION

# ስለ የአይፓድ/iPad የተመለከተ ጥቅል ማብራሪያ

የአይፓድ/iPadዎ በአፕል በማሸጊያ ሳጥኑ ውስጥ ከተከተተ የወረቀት መመሪያ ጋር መጥቷል። የአፕልን የተሟላ የአይፓድ/iPad የተጠቃሚ መመሪያ በኦንላይን ከ support.apple.com ላይ ያገኛሉ። ይህ እርስዎ የሚያነቡት መመሪያ አንዳንድ ተመሳሳይ መረጃዎችን የያዘ ሆኖ በቀላል ፎርማት የተዘጋጀ ነው። መመሪያው በተጨማሪም ተጨማሪ ጠቃሚ ሆነው ሊያገኟቸው የሚችሏቸው መረጃዎችን ይዟል። ማስታወሻ: በዚህ የአይፓድ/iPad ማብራሪያ መመሪያ ስር የማያውቋቸው ቃላት ወይም ሙያዊ ቃላት የሚያጋጥሙዎ ከሆነ እባክዎ የአይፓድ/iPad የቃላት ፍቺ የሚይዘው የመጨረሻውን ገጽ ይመልከቱ።


## በተኖች/ፖርቶች:







## አይፓድ/iPadዎን እንዴት ቻርጅ እንደሚያደርጉ:




ስለ አይፓድ/iPad መሰረታዊ አጠቃቀም የተመለከቱ አንዳንድ ጠቅላላ መረጃዎችን የያዘ የ35 ደቂቃዎች ጥሩ የዩቲዩብ ቪዲዮ እዚህ ላይ ቀርበልዎታል:

https://bit.ly/iPad-Basics

# የአይፓድ/iPadዎን እንዴት እንደሚያስተካክሉ/እንደሚሞሉ

1. **ያብሩ**: የአይፓድ/iPadዱን የሀይል በተን በመጫን የአፕል አርማ እስከሚመጣልዎ ድረስ ይዘው ይቆዩ፡፡

2. **ቀጥሎ**: በብዙ ቋንቋዎች የሚመጣ "Hello" የሚል ሰላምታ ያያሉ፡፡ ለመጀመር በስክሪኑ ላይ የሚታዩዎትን መመሪያዎች ይከተሉ፡፡ (ማየት የተሳነዎ ወይም የማየት ችሎታዎ አነስተኛ ከሆነ ከ ሄሎ/ Hello ስክሪን ላይ VoiceOver ወይም Zoomን ማብራት ይችላሉ)፡፡ በሚጠየቁበት ወቅት ቋንቋዎን ይምረጡ፡፡ ከዚያም ሀገርዎ (ዩኤስ) ላይ ይጫኑ፡፡ ይህ ቀን፣ ሰአት፣ ግንኙነቶች እና ሌሎችንም ጨምሮ በመረጃው ገጽታ ላይ ተጽእኖ ይፈጥራል፡፡ ቀጥለውም የመሙላት ተሞክሮዎን የአዲሱን አይፓድዎን/iPad አጠቃቀም በማሻሻል ሊረዱዎ የሚችሉትን የመጠቀሚያ አማራጮችን/ Accessibility Options ለመሙላት ሰማያዊ ቀለም ያለውን የመጠቀሚያ በተን ይጫኑ፡፡





ለመቀጠል ከስክሪኑ በታች የሚገኘውን "Set Up Manually" የሚለውን ይጫኑ፡፡

3. **ያሰሩ/ያስጀምሩ**: መሳሪያዎን ለማሰራት/ለማስጀመር እና መሙላትዎን/ማስተካከልዎን ለመቀጠል የWi-Fi ኔትወርክ፣ የሞባይል ስልክ ኔትወርክ ወይም iTunes ማገናኘት ይጠበቅብዎታል፡፡ ለመጠቀም የሚፈልጉትን የ Wi-Fi ኔትወርክ ይጫኑ ወይም የተለየ አማራጭ ይጠቀሙ፡፡



4. **የመሙያ/ማስተካከያ Touch ID**: በዚህ አገልግሎት አማካኝነት መሳሪያዎን ለመክፈት እና ግዢዎችን ለመፈጸም የጣት አሻራዎን መጠቀም ይችላሉ። ይቀጥሉ/ Continue የሚለውን ይጫኑ እና መመሪያዎቹን ይከተሉ፣ ወይም "Set Up Later in Settings" የሚለውን ይጫኑ።


5. **የሚስጥር መግቢያ ይፍጠሩ**: የመረጃዎን/ዳታዎን ደህንነት ለመጠበቅ ባለ ስድስት አሀዝ/ፊደል የሚስጥር መግቢያ ይፍጠሩ። እንደ Touch ID እና Apple Payየመሳሰሉ አገልግሎቶችን ለመጠቀም የሚስጥር መግቢያ ያስፈልግዎታል። ባለ አራት አሀዝ/ፊደል የሚስጥር መግቢያ መፍጠር፣ የሚስጥር መግቢያዎን ማስተካከል የሚፈልጉ ወይም ምንም የሚስጥር መግቢያ እንዳይኖርዎ ማድረግ የሚፈልጉ ከሆነ "Passcode Options" የሚለውን ይጫኑ።




6. **በApple IDዎ ይመዝገቡ**: የApple IDዎን እና የሚስጥር መግቢያዎን ያስገቡ፣ ወይም "Forgot password ወይም የApple ID የሉዎትም?" የሚለውን ይጫኑና ከዚህ በመነሳት የApple IDዎን ወይም የሚስጥር መግቢያዎን መልሰው ማግኘት፣ የApple ID መፍጠር ወይም ቆይተው መፍጠር ይችላሉ። ከአንድ በላይ የApple ID የሚጠቀሙ ከሆነ " ለiCloud እና iTunes የተለዩ የApple IDዎችን መጠቀም ይፈልጋሉ?" የሚለውን ይጫኑ። በApple IDዎ በሚመዘገቡበት ጊዜ ቀደም ሲል ይጠቀሙበት ከነበረው መሳሪያ የማረጋገጫ ኮድ ማሳሰቢያ ሊመጣልዎ ይችላል።




7. **ፈጣን ወቅታዊ ማሻሻያዎችን ይክፈቱ እንዲሁም ሌሎች አገልግሎቶችን ይሙሉ** : በቀጣይ ስክሪኖች ላይ ለአፕል አዘጋጆች can decide whether to መረጃ ስለማካፈል ሊወስኑ እና ለiOS ለፈጣን ወቅታዊ ማሻሻያዎችን እንዲጭን ሊፈቅዱ ይችላሉ።




8. **Siri እና ሌሎች አገልግሎችን ይጫኑ**: እንደ Siri የመሳሰሉ አገልግሎቶች ወይም መጠቀሚያዎችን እንዲሞሉ ወይም እንዲያሰሩ ይጠየቃሉ። Siri ድምጽዎን ለማወቅ እንዲያስችለው ጥቂት ሀረጎችን እንዲናገሩ ይጠየቃሉ። የሚመዘገቡት በApple IDዎ ከሆነ እና አማራጭ የ Apple Pay እና iCloud Keychainን መሙላት የሚፈልጉ ከሆነ በአይፓዱ/ iPad ላይ የሚሰጡትን መመሪያዎች ይከተሉ።



9. **የስክሪን ሰአት/Screen Time እና ጨማሪ የማሳያ አማራጮችን ይሙሉ**: የስክሪን ሰአት/Screen Time እርስዎ እና/ወይም ልጅዎ መሳሪያዎን ምን ያክል ጊዜ እንደተጠቀማችሁ መረጃ ይሰጥዎታል። ሰዐት መሙላቱ በተጨማሪም ለአለታዊ የመተግበሪያ አጠቃቀምዎ ጊዜ እንዲወስኑ ያስችልዎታል። የስክሪን ሰዐት/ Screen Time ከሞሉ በኋላ በነባሪ/ Home ስክሪንዎ ላይ የምልክቶች/አይከኖች እና ጽሁፍ መጠንን ለማስተካከል Display Zoomን መጠቀም ይችላሉ።




10. **ያብቁ/ያጠናቁ**: አይፓድ/ iPadዎን መጠቀም ለመጀመር "Get Started" የሚለውን ይጫኑ። የመጠባበቂያ መረጃ በመፍጠር የዳታዎን አስተማማኝ ኮፒ ይያዙ እንዲሁም ከiPad ሳጥንዎ ጋር በሚመጣልዎ የተጠቃሚ መመሪያ ውስጥ ስላሉ ተጨማሪ አገልግሎቶች ይወቁ።

11. **አይፓድ/iPadዎን ቻርጅ ያድርጉ**: የባትሪ ምልክቱ/አይከኑ ዝቅ ሲል ቻርጅ ማድረጊያዎን ይሰኩ። አይፓድ/ iPad ቻርጅ የሚያደርገው የባትሪ ምልክቱ 'lightning bolt' ሲኖረው እንደሆነ ያውቃሉ።



12. **አይፓድ/ iPadዎን ያጥፉ**: በ አይፓድ/ iPadዎ የላይኛው የቀኝ ማእዘን ላይ የሚገኘውን **On/Off/Sleep** በተንን ተጭነው ያዙ። በተኑን ከስክሪኑ ላይ ብርሀን/ Slide እስኪጠፋ ድረስ ይዘው ይቆዩ። **ለማጥፋት ማንቀሳቀሻውን** ወደ ቀኝ ጎን እስከ ጥግ ያንቀሳቅሱ።


ያስታውሱ ይህን መረጃ እና ተጨማሪም በዲጂታል አካታች/ Digital Inclusion ድረገጻችን:

cv-atlab.org/Digital-Inclusion ላይ ያገኛሉ።

# የአይፓድ/iPad ገበታዎች/ሴቲንጎች


የሴቲንጎች መተግበሪያውን ነባሪ ገበታው/Home ስክሪኑ ላይ ያገኛሉ። ሆም ስሪኑ ብዙ ነገሮችን የሚያደርጉ ማውጫዎችን ይይዛል። ለምሳሌ:

- ታብሌትዎ እንዴት እንደሚሰራ መቀየር
- የApple IDዎን እና የApp Store ምዝገባዎችን መቆጣጠር
- የተወሰኑ ይዘቶችን መዝጋት
- መሳሪያዎን እርስዎ እና/ወይም ቤተሰብዎ እንዴት እንደምትጠቀሙ መቆጣጠር
- ማስታወቂዎችን፣ ግላዊነት እና የሚስጥር መግቢያ መሙላት
- Wi-Fi ማብራት/ማጥፋት
- የጀርባ እይታ/ “wallpaper” መሙላት
- የስክሪንዎን የብርሀን መጠን መቀየር
- እና ተጨማሪ ሌሎችም!



# የመጠቀሚያ ሴቲንጎች

አይፓድ/ iPad ለእይታ፣ አካልና እና እንቅስቃሴ፣ ለመስማትና የመማር ፍላጎቶችና ምርጫዎች ድጋፍ የሚያደርጉ ብዙ የመጠቀሚያ አገልግሎቶች አሉት። ወደ ሴቲንጎች ይግቡ እና የመጠቀሚያ/ Accessibility ምልክትን ይፈልጉ:





ከዚያም ከሚከተሉት አገልግሎቶች መካከል የትኛውንም ይምረጡ። የእነዚህ የእያንዳንዱን ልዩ መመሪያዎች እና ቪዲዮዎች/ሊንኮች ከዲጂታል አካታች/ Digital Inclusion ድረገጻችን ላይ በኦንላይን በ: www.cv-atlab.org/digital-inclusion ያገኛሉ።


| **እይታ/አይን** | **አካል እና እንቅስቃሴ** | **መስማት/ጆሮ** |
|---|---|---|
| ድምጽ/Voice Over | መንካት/Touch | የመስሚያ መርጃ መሳሪያዎች/Hearing Devices |
| Zoom | የፊት ID እና ትኩረት | ድምጽ ለይቶ ማወቂያ |
| ምስል ማጉያ | የመቀየሪያ መቆጣጠሪያ | RTT/TYY |
| ማሳያና የጽሁፍ መጠን | የድምጽ መቆጣጠሪያ | ድምጽ-እይታ/ AudioVisual |
| እንቅስቃሴ | ሆም ወይም የላይኛው በተን | ንዑስ ርዕሶችና የግርጌ ማብራሪያዎች |
| የንግግር ይዘት | የApple የቲቪ የርቀት መቆጣጠሪያ | **ጠቅላላ** |
| የድምጽ ዝርዝሮች/ማብራሪያዎች | የጠቋሚ መቆጣጠሪያ | ቁጥጥር የሚደረግበት አጠቃቀም |
| | ኪቦርዶች | Siri |
| | አፕል ፔንስል/Apple Pencil | የመጠቀሚያ አቋራጭ መግቢያ/Accessibility Shortcut |

# ኢሜይል መሙያ

እንደ iCloud፣ Google ወይም Outlook የመሳሰሉ የኢሜይል አቅራቢዎችን የሚጠቀሙ ከሆነ የመልዕክት ሴቲንጎች በፍጥነት የኢሜይል አካውንትዎን ከኢሜይል አድራሻዎና የሚስጥር መግቢያዎ ጋር ይሞላሉ፡

1. ወደ ሴቲንጎች ይግቡ > ወደ ታች ወደ **መልዕክት ያንቀሳቅሱ** > ከዚያም **አካውንቶችን ይጫኑ**።
2. በመጀመሪያ **Add Accountን ይጫኑ**፣ ቀጥለውም የኢሜይል አቅራቢዎን ይምረጡ። የኢሜይል አቅራቢዎ የማይመጣልዎ ከሆነ አካውንትዎን በማኑዋል ለማስገባት ሌላ/Other የሚለውን ይጫኑ።)
3. የኢሜይል አድራሻዎን እና የሚስጥር መግቢያዎን ያስገቡ።
4. ቀጥለው **Nextን** ይጫኑ እና መልዕክቱ/ Mail የእርስዎን የግል አካውንት/መረጃ እስከሚያረጋግጥ ድረስ ይጠብቁ።
5. ከኢሜይል አካውንትዎ ላይ እንደ የስም ማውጫዎች ወይም ቀን መቁጠሪያዎች የመሳሰሉ መረጃዎች ይምረጡ።
6. ከዚያም **Saveን ይጫኑ**።




# FaceTimeን መሙላት

በFaceTime መተግበሪያ ላይ ለጓደኞችዎና ቤተሰብዎ የቪዲዮ ወይም የድምጽ ጥሪዎች ማድረግ ይችላሉ። የፊት ለፊቱን ካሜራ በመጠቀም ፊት ለፊት እየተያዩ ማውራት ይችላሉ። በዙሪያዎ የሚገኙ ነገሮችን ለሚያዋሩት ሰው ለማሳየት የኋለኛውን ካሜራ ያብሩ።

1. ወደ > FaceTime ሴቲንጎች ይግቡ እና ከዚያም FaceTimeን ያብሩ።
2. በ FaceTime ጥሪዎች ወቅት በቀጥታ ፎቶዎችን ለመውሰድ መቻል የሚፈልጉ ከሆነ FaceTime Live Photos የሚለውን ይክፈቱ።
3. FaceTimeን ለመጠቀም ስልክ ቁጥርዎን፣ የአፕል/ Apple IDዎን ወይም የኢሜይል አድራሻዎን ያስገቡ።



# የኦንላይን/ኢንተርኔት ደህንነት

በአይፓድ/ iPad ላይ መጠቀም የሚችሏቸው ብዙ የተለያዩ የኢንተርኔት ማሳያዎች/ማውጫዎች አሉ። አይፓድ/ iPad የሚቀርብልዎ በቅድሚያ ሳፋሪ/Safari (ከላይ የሚመጣው ሰማያዊ የኮምፓስ ምልክት) ተጭኖበት ነው። የሚመርጡት የትኛውንም የኢንተርኔት ማሳያ/ማውጫ ይሁን ከዚህ በታች የቀረቡት 10 የኢንተርኔት ደህንነት ፍንጮች ናቸው፡

1. ኢንተርኔት መጠቀም ለእርስዎ አዲስ ከሆነ የሚያምኑትን ሰው እንዲረዳዎ ይጠይቁ።
2. ‹እውነት ለመሆን በጅጉ የማያሳምኑ› (አጭበርባሪዎች) የኢሜይል ግብዣዎችን ይሰርዙ።
3. የግል መረጃዎን በኦንላይን አያካፍሉ።
4. የግላዊነት ሴቲንጎች እና የመተግበሪያ ግላዊነት ፖሊሲዎችን አንብበው ይረዱ።
5. የሚስጥር መግቢያዎችዎን በፍጹም አይግለጹ (የሚስጥር መግቢያዎችዎን በሚስጥር ይያዙ/ለሚያምኑት ሰው ብቻ ይግለጹ)
6. የሆነ ነገር በኦንላይን ከመናገርዎ በፊት ያስቡ። የሚናገሩት ነገር በጣም ለብዙ ሰዎች ሊደርስ ይችላል።
7. የሆነ ሰው በኦንላይን እርስዎን የሚያበሳጭዎ ነገር የሚናገር ከሆነ ይህን ለሚያምኑት ሰው ይንገሩ።
8. ሊንኮች ሊታመኑ የሚችሉ መሆናቸውን ካላወቁ በስተቀር ሊንኮችን አያውርዱ ወይም አይጫኑ።
9. የህዝብ የሆነ Wi-Fi (ለምሳሌ የሻይ-ቡና መሸጫ ቦታ) በሚጠቀሙበት ወቅት የግል ወይም የፋይናንስ መረጃዎን ድረገጽ ላይ አያስገቡ።
10. ሶፍትዌርዎ ላይ በየጊዜው ማሻሻያ ያድርጉ

ስለ ኦንላይን ደህንነት በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት: www.usa.gov/online-safety ን ይጎብኙ።

ያስታውሱ፡ ይህን መረጃም ሆነ ተጨማሪ ነገሮችን ከዲጂታል አካታች/ Digital Inclusion ድረገጻችን ላይ በ:

cv-atlab.org/Digital-Inclusion ያገኛሉ።

# የአይፓድ/iPad የቃላት ፍቺዎች

**App**: የ “መተግበሪያ።” ምህጻረ ቃል ነው። በአይፓድ/ iPadዎ ስክሪን ላይ ያሉት እያንዳንዱ ምልክቶች እንደ ኢሜይል፣ ኢንተርኔት ማውጫ፣ ወዘተ የመሳሰሉ ተግባሮችን የሚሰሩ “app” ወይም ፕሮግራም አሉ።

**የApple ID**: የኢሜይል አድራሻዎን እና የመረጡት የሚስጥር መግቢያዎን የሚጠቀም ልዩ የተጠቃሚ ስም እና የሚስጥር መግቢያ ነው። ይህ አይፓድ/iPadዎን ለመሙላት እና ነጻ መተግበሪያዎችን ጨምሮ መተግበሪያዎችን ለማውረድ ያስፈልጋል።

**Bluetooth**: እንደ ኪቦርዶች፣ ስፒከሮች፣ Apple pencil፣ ሄድፎኖች ወይም ሌሎች ተጓዳኞችን የመሳሰሉ መገልገያዎችን ከአይፓድ/ iPad ጋር ማገናኛ ገመድ አልባ ዘዴ ነው። የBluetooth አገልግሎት መስጫዎች በሴቲንግ ማውጫ ውስጥ ከዚያም ከ“Bluetooth” ታብ ከአይፓድ/ iPadዎ ጋር ሊገናኙ ይችላሉ።

**የሄድፎን መሰኪያ/Headphone Jack**: በአይፓድ/iPad የላይኛው የግራ ጎን ጥግ ላይ የሚገኝ ትንሽ ክብ መክፈቻ ያለው የሄድፎን ገመዶችን ከአይፓድ/ iPad ጋር የሚያገናኝ ነው።

**Home Button**: ከአይፓድ/ iPad የፊት ለፊት የታችኛው መካል ክፍል ላይ የሚገኝ ክብ፣ ነጥብ መጠን ያለው ካሉበት ስክሪን ወጥተው መተግበሪያዎችዎ ወዳሉበት ወደ “home” ለመመለስ ለመጫን የሚያገለግል ነው። አንዴ ስክሪንዎ ሲጠፋ አይፓድ/iPad ዎን መልሰው ካበሩት በኋላ ሊጫኑት ይችላሉ። በተጨማሪም አይፓድ/iPad ዎን ለመክፈት Touch ID በሚጠቀሙበት ወቅት ሆም በተን የጣት አሻራዎን የሚያሳርፉበት ቦታ ነው።

**የኢንተርኔት/ድረገጽ ማውጫ/Internet/Web Browser**: ኢንተርኔት/ድረገጽ ፈልገው በመግባት ለመጠቀም የሚያስችልዎ ፕሮግራም ወይም መተግበሪያ ነው። እጅግ የታወቁት የኢንተርኔት ማውጫዎች Safari፣ Google Chrome፣ እና Firefox ናቸው።

**iOS**: የአይፓዶች/ iPads እና አይፎኖች/ iPhones የአፕል ማሰሪያ ሲስተም/Apple Operating System ነው። ማሰሪያ ሲስተም ኮምፒውተርዎ ወይም መሳሪያዎን የሚያስነሳ/የሚያሰራ የሶፍትዌር መርሀግብር ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ መጨረሻው ላይ የሚጠቀሙትን ሲስተም አይነት/ትውልድ የሚነግሩዎ ቁጥሮች አሉት። ለምሳሌ፡ በአሁኑ ወቅት እግ የቅርቡ የ iOS ትውልድ iOS 14.2 ነው። በየተወሰነ ጊዜ በሴቲንግ ማውጫዎ ላይ “General” ከሚለው ስር በመግባት የማሰሪያ ሲስተምዎ ላይ ማሻሻያ ማድረግ አለብዎ።

**የመብራት ገመድ/Lightning Port**: በአይፓድ/ iPadዎ የስረኛው ማዕከላዊ ጠርዝ ላይ የሚገኝ የቻርጅ ማድረጊያ ገመድ ከአይፓድ/ iPad ጋር የሚገናኝበት ትንሽ፣ ልሙጥ ጫፍ ያለው ገመድ ነው። በተጨማሪም አዲስ ከአፕል ሸቦ ጋር የተገናኙ ማስገቢያዎችም እዚህ ላይ ሊገናኙ ይችላሉ።

**የመብራት አገናኝ/Lightning Connector**: አይፓድ/ iPad ቻርጅ ለማድረግ ወይም እንደ ኮምፒውተር ካሉ ሌሎች መሳሪያዎች ጋር ለማገናኘት የሚያገለግል ገመድ ነው። አንደኛው ጎኑ ትንሽና ልሙጥ ሲሆን ከአይፓድ/ iPad’s የመብራት ገመድ ጋር ይገጠማል። ሌላኛው ጎኑ ተለቅ ያለ አራት ማእዘን የUSB ማገናኛ ሲሆን ቻርጀር ወይም በኮምፒውተር ወይም ሌላ መሳሪ የUSB ገመድ ላይ ይሰካል።

**Phishing:** የኢሜይል ወይም ኢንተርኔት ማጭበርበሪያ አይነት ነው። የphishing ማጭበርበሪያ በአብዛኛው በኢሜይል ወይም ድረገጽ ላይ የሚመጣ ከተጫኑት የግል የተጠቃሚ መረጃዎን ሰርቆ ሊወስድ የሚችል ሊንክ ወይም መልዕክት ነው። ከማያውቁት ሰው ወይም መመዝገብዎን ከማያስታውሱት የኢሜይል ዝርዝር የኢሜይል መልዕክት የሚመጣልዎ ከሆነ ጥንቃቄ ያድርጉ። አጠራጣሪ የመሰሉዎትን የትኛውንም ሊንኮቸወ ወይም መልዕክቶች አይጫኑ።

**የሀይል በተን/Power Button:** በአይፓድ/ iPadዎ የላይኛው የቀኝ ጥግ ላይ የሚገኝ ልሙጥ አራት ማዕዘን በተን ነው። ይህ በተን አይፓድ/ዎን ስክሪንዎ አይፓዱ መጥፋቱን እስከሚያሳይዎ ድረስ በተኑን ተጭነው በመያዝ ለማጥፋት/ለማብራት የሚያገለግል ነው። በተኑን አንድ ጊዜ መጫን የአይፓድዎ ስክሪን እንዲበራ ወይም ብርሀኑ እንዲጠፋ ያደርጋል።

**Siri:** በአይፓድ/ iPadዎ ላይ የሚገኝ ጥያቄዎችን ለመጠየቅ እና ትእዛዞችን ለመስጠት ድምጽ መጠቀም የሚችሉበት ፕሮግራም ነው። Siri ጥያቄዎችን በቃል መቀበል እንዲሁም መተግበሪያዎች መክፈትን፣ የስልክ ጥሪዎች ማስቀመጥን፣ የጽሁፍ መልእክት እና ኢሜይሎች መጻፍ ወይም ማንበብን ወይም ለጥያቄዎች በኢንተርኔት መልስ መስጠትን ጨምሮ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል።

**Touch ID:** አይፓድ/ iPadዎን በጣት አሻራዎ ለመክፈት የሚያስችሉዎ የአፕል የደህንነት ሴቲንግ ነው። የመሙያ መመሪያዎችን ከላይ ይመልከቱ። አይፓድ/ iPadዎን ከሞሉ በኋላ ከፈለጉ ተጨማሪ የጣት አሻራዎችን ማስገባት ይችላሉ።

**Wi-Fi:** (የ 'wireless fidelity' ምህጻረ ቃል) እንደ አይፓዶች/ iPads፣ ስማርት ስልኮች፣ ኮምፒውተሮች እና ፕሪንተሮች የመሳሰሉ መሳሪያዎች ኢንተርኔት እንዲጠቀሙ እና ተመሳሳይ የ Wi-Fi አገልግሎት/ኔትወርክ ላይ ከሆኑ እርስ በርሳቸው እንዲገናኙ ለማድረግ የሚያስችል በግዝ የሚገኝ አገልግሎት ነው። Wi-Fi በመኖሪያ ቤትዎ ሊያስገቡ ወይም አገልግሎቱን ከሻይ-ቡና መሸጫ ቦታዎች ወይም ትላልቅ መደብሮች (ለምሳሌ የመጠጥ ማከፋፈያ) ሊጠቀሙ

# ለሚከተሉት የቀረበ ምስጋናና እውቅና:

በsupport.apple.com ለሚገኘው at [የአፕል የኦንላይን ድጋፍ መስጫ/Apple Support online](support.apple.com) ። አብዛኞቹ የዚህ የአይፓድ/iPad ማብራሪያ መስጫ መመሪያ ይዘቶች በአፕል ድጋፍ/ Apple Support ስራ ላይ የተመሰረቱ ናቸው።

የፖርትላንድ ከተማ እና የCARES Act ፕሮጀክት COVID-19 በመጀመሪያ ደረጃ ላይ በሚገኙ ማህበረሰቦች ላይ ባሳደረው ተጽእኖ የተነሳ በፖርትላንድ ከተማ ምክር ቤት በጸደቀው በCARES Act በአካባቢ የማገገሚያ ፈንድ ህገደንብ/Local Relief Funds Ordinance አማካኝነት ድጋፍ አድርገዋል። ይህ የገንዘብ እርዳታ ለአይፓዶች/iPads፣ ለአጋዥ ቴክኖሎጂ፣ ስርጨጭት እና በመቶዎች ለሚቆጠሩ የፖርትላንድ ነዋሪዎች ስልጠና ተከፍሏል። ልዩ ምስጋናችንን ለ COVID-19 ምላሽ የዲጂታል ክፍል የስራ ቡድን/ COVID-19 response Digital Divide Work Group እና ለሁሉም ላደረጓቸው ጥረቶች እናቀርባለን።

ሕዳር 1, 2016 ዓ.ም